“አላህ ወአክበር” !





# “አላህ ወአክበር” !

(ለኢትዮጵያውያን ሙስሊም ወገኖቼ የሙብት ትግል፣ የአንደኛ ዓመት መታሰቢያ ትሁን)

“አላህ ወአክበር” አለ ሙስሊም - አምላክ ይክበር ሲል አስተጋባ፣
የሰላም፣ የፍቅር፣ የሙብት . . .፣ የነጻነት፣ ህይወት ፍለጋ!
ሶላቱን እየሰገደ - ለ’ሰማያዊ’ አባቱ ክብር፣
ለስርዓተ - ደንቡ ተገዝቶ - ለሚኖርባትም ምድር፣
በደሉን እየዘረዘረ - በግልጽ ቋንቋ በማያሻማ፣
በሕብረ - ድምጽ አጅቦ - አቤቱታውን አሰማ





. . ታሪካዊ ማንነቱን፣ የትውልዶች እምነቱን፣
የነብዩን (ወ.ሰ) ምክር ጠቅሶ፣ የቢላልን ወኔ ወርሶ፣

ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነኝ አለ፣ “አላህ ወአክበር” !
“እስላም - ሰላም እየሰበከኹ በምድሪቱ ለዘላለም እምኖር” !

. . ይህን ሃቅ ባደባባይ - ሰምቶ እንዳልሰማ የካደ፣
ህሊናውን የሸቀጠ - በደም ልክፍት ያበደ፣
ልማደኛው ወያኔ ግን አድብቶ ተናካሹ፣
ሰብዓዊነት - አልባ - ያራዊት “ህግ” አንጋሹ፣
ጆሮ - ዳባ ልበስ ብሎ - ለሰላማዊው ትግል ጥሪ፣
“ጅሃድ . .፣ሽብር . .፣ ‘ቅብርጥሴ’ ” ይላል— ራሱ ሆኖ ሳለ አሸባሪ!





“መፍትሔ አፈላላጊ” ብሎ - ኮሚቴ ሲመሰርትማ፣
መስሎት ነበር ሕብረተሰብ . . .
ፍትህ ያለ፣ እምነት ያለ፣ መንግስት ያለ፣ ስርዓት ያለ . .
ጥያቄውን የሚሰማ፤

የሰው ስጋ የለበሰ - እምነት ማተብ የበጠሰ፥
እንሰሳዊው ወያኔ - ምላሹ ሆነ የጭካኔ፤
ኮሬንቲውን አቀጣጥሎ. . .እቶን እሳት አንድዶ፣
ሂትለራዊ “ኦሽዊትዝ” የሰቆቃ “ቻንበሩን” ገንብቶ፣
ከ”ማዕከላዊ” . . እስከ አቃቂ - የስቃይ ማዕከል መስርቶ፣
በ”ዘር - ፍሬ” ጠርሙስ አንጠልጥሎ - ጺም ነጭቶ፣ ጥፍር ነቅሎ፣
ጨለማ ቤት አጉሮ . . .፣ - በሰንሰለት ጠፍሮ . .፣
ባለጊዜ- ባለብረት - ንጹሃንን ፊጥኝ አስሮ . . .፣
በሰው ስቃይ ይቀልዳል . .፣
የምጸቱ መጨረሻ - ለ”ኢቲቪ” ምስል ይቀርጻል።






. . . ይቀጥላል . . ! ትግል ጉዞ፣ - እጅ - ለእጅ ተያይዞ!
አይበገርም! ለስቃይ - የድል ምዕራፉን እስኪያይ!
እብሪተኛ እስኪተነፍስ፣ እስኪሙዋሸሽ ልኩን አውቆ፣
ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነጻነት . .፣ እስኪያበራ ከጽንፍ - አጽናፍ ደምቆ፣
ዜጎች ሁሉ ባገራቸው ኮርተው - እስኪራመዱ ደረታቸውን ነፍተው፣
. . ይቀጥላል! ሰላማዊ ትግል ይቀጥላል . . . !
መብት ረጋጭ፣ ዘረኛውን ያቃጥላል፤
ንጹሃንን ነጻ ያወጣል! !
ቀርባለች ያቺ ዕለት፣ የብሩህ ተስፋ ቀን፣ እሚያግዳት ሃይል የለም፣
አላሁ ወአክበር! ይመስገን እግዚአብሔር! ይክበር ለዘላለም!





---

ጌታቸው አበራ
የካቲት 2005 ዓ/ም
(ፌብሯሪ 2013)